ጠጅን በብርሌ ነገርን በምሳሌ

ከኦቦ አራዳ አባ ሻውል

ህዳር 12፣2008 ዓ.ም.

ከላይ እንደ ተጠቀሰው የአበው ምሳሌ፤ ፖለቲካና ኤኮኖሚ አይለያዩም ለማለት መሰለኝ፡፡ ፖለቲካ ነገርን በምሳሌ ለማመላከት ሲሆን፤ ጠጅን ደግሞ በብርሌ ኤኮኖሚን ለማመላከት ይመስላል፡፡ ይህንን ምሳሌ ያለው ማን ፈላስፋ ወይ ፕሮፌሰር ነው? ለአባባሉ ባለቤት አለው? ባዩስ ፖለቲከኛ ነው ወይ የኪነት ሰው? የመሳሰሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በኤትዮጵያዊነት ታሪክና ባሕል ኪነት የብዙሀኑ ንብረት እንጂ የግል እንዳልነበረ ያስረዳናል፡፡ ሆኖም ዘመናዊ የኮለጅ ትምህርት ሲስፋፋ ካሪክለሙ በግዕዝ መሆኑ ቀርቶ በላቲን ፊደል መማማር ተጀመረ፡፡ የአገሬው ተወላጅ አስተማሪውም ተማሪውም በግዕዝ ፊደላት መግባባት ተጠየፈ፡፡ ከ ሀሐኀ እስከ ፐፐፐ ማለት ድንቁርና ሆነና አረፈው፡፡ በአንፃሩ AAA-ZZZ የሚል ተተካ፡፡ እነደዚሁ ሲያዩት በላቲን ሲጻፍ የቀለለ ሆነ ሊታይ ይችላል ነገር ግን ጠለቅ ብሎ ለሚመራመረው ሰው ከ ሀ-ፐ ያጠና ሰው ለማንበብም ሆነ ለመጻፍ ይቀለዋል፡፡ መዝገበ-ቃላት አያስፈልገውም ወይንም ካፒታል፡፡ ከ A-Z ተጠቅሞ የተማረ ሰው ግን ለአንዴም ለሁሌም ምሁር ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፤ እድሜው ሙሉ ሲወድቅ ሲነሳ ይኖራታል፡፡ በዚህ ምክንያት ይመስለኛል ሐፋሽ ሕዝብ ከምህሮ አእምሮ እያለች የምትፎክርብን፡፡ ምሁር አካል ደግሞ በበኩሉም ሰፊው ሕዝብ መሀይም ነው እያለ ራሱን ያጽናናል፡፡

ስለሆነም በኤርትራና ኢትዮጵያ ሁለት አይነት ምሁራን ተፈጠሩ፡፡ እነሱም በፊደልና በላቲን የተማሩ፤ ወይንም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ምሁራንና ፅንሐተ-ምሁራን ተብለው የሚታወቁት፡፡ በምሳሌ ለማስረዳት እንደሚከተለው ፕሮፌሰር መስፍን ወ. ማርያምን አመለካከት እንውሰድ፡-

ቁም ነገሩ

የአገር መኖር ወይም አለመኖር

የአገርን ህልውና ለመጠበቅ ከጠላት መከላከል ዋና ሥራ ሆኖ ሌላ ሥራ ሁሉ ተዘንግቶ፤ወይም ትኩረት ሳይሰጠው ቀርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቀር ሆነ፤ የአገርን ህልውና መጠበቁ የነገሥታቱና የሕዝቡ ዋና ተግባር ሆኖ መዕተ-ዓመታት ተቆጠሩ፤ ሕዝቡ ህልውናን የሚጠብቀውን ጀግንነትና አርበኝነት እያወደሰና እያሞገሰ፤ እየሸለመና እያከበረ መኖርን ባህሉ አደረገ፤ ይህ ባህል ጀግንነትና አርበኝነትን ማክበር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብም እርስበርሱ የሚመዛዘንበትና የሚከባበርበት መለኪያ ሆኖት ቆየ፤ ትዳርም ሆነ ንብረት፤ ተሰሚነትም ሆነ የኃላፊነት ክብር መፍለቂያ ጀግነነትና አርበኝነት ነበሩ፡፡

ይህንን ጥቅስ የተወሰደው ከአዳፍኔ ፍርሃትና መክሸፍ መፅሐፍ ከፕሮፌሰር መስፍን የተወሰደ ነው፡፡ እንግዲህ መፅሐፉን ያላያችሁ ሰዎች በሽፋኑ ላይ የሶስት መሪዎች ፎቶግራፍ አለ፡፡ እነሱም አንደኛ የዓፄ ኀይለ ሥላሴ፤ ሁለተኛ የፐረዝደንት መንግሥቱ ሀይለማርያም ሲሆኑ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የጠቅላይ መለስ ዜናዊ ናቸው፡፡የፎቶግራፎቻቸው ይዘት የሐዘን መደፋት ሳይሆን ፍርሐትን ለማሳየት መሰለኝ፡፡ ሶስቱም ፈሪዎች ናቸው ለማለት መሰለኝ፤ ስለፈሪነታቸው ከፕሮፌሰር በላይ የሚያወቃቸው ሰው የለምና በዚህ አንከራከርም፡፡ እንደእኔ ፕሮፌሰር መስፍን ተራ ምሁር ስለሆኑ ማለትም ፅንሐተ-ምሁር አካል ስላልሆኑ አይፈረድባቸውም፡፡ (በነገራችን ፅንሐተ- ምሁራን ማለት- በፅንሰ- ሀሳብ ፤በንደፈ-ሀሳብ-ና-በተግባር የተካኑ ናቸው) armed with Concept-Theory-Application.

ፕሮፌሰር መስፍን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግራፊካላዊ አቀማመጥ በቲዮሪ ካልሆነ በተግባር ያዩት አልመሰለኝም፡፡ አሊያም በፖለቲካል ጀግራፊ ብቻ ተገንዝበው ሕዝቡ እንዲህ ነው እንዲያ ነው እያሉ ባይፅፉ ይከበሩ ነበር፡፡ ለነረሱ ፕሮፌሰሬ ሴኩሪቲ ምን ማለት እንደሆነ ሊገልፁልን ይችላሉ? የኢትዮጵያ ሕዝበስ ስለ ሰኩሪቲ ያለው ግንዛቤ ያወቀዋል ብለው ያምናሉ? ደህንነትና

ሴኩሪቲ ልዩነቱን ቢነግሩኳ? ለብሕራዊ ሴኩሪቲ ሁሉም አገሮች ብዙ ባጀት ይመድባሉ ለምሳሌ የአሜሪካ መንግሥት በየአንዳንድ ዶላር ሰማንያ ሳንቲም ገደማ ወጪ ያደርጋሉ። የኛዎቹስ ለደህንነታቸው ብቻ ወጪ ያደርጋሉ እንጂ ለአገር ሴኩሪቲ ባጀት የላቸውም። ስለዚህ ፕሮፌሰርም ብለውታል እያንዳንዱ ሰው አገሩን ከባእድ ከሚላቸው እየጠበቀ የኖረ ሕዝብ ነው። በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያና የአሁና ኤርትራ አንጡራ ሀብታቸውንና መሬታቸውም ሆነ ቤተሰቦቻቸው በባጀት ሳይሆን በደመ ነበስ አገሪትዋን ለራሳቸውም ሳይተቀሙባት አልፈዋል። ይህም ማለት ድንግልዋን አገር ከትውልድ ለትውልድ እያሉ የ**ኢትዮጵያ ሕዝብም እርስበርሱ የሚመዛዘንበትና የሚከባበርበት መለኪያ ሆኖት ቆየ**፤ ብለው ያሰፈሩት መልካም አባባል ነው። ታዲያ ለኔ ይቅርብኝ ለትውልድ ይሁን እያሉ ማስተላለፍ ምኑ ላይ ነው ኃላ-ቀርነቱ። እንግዲያውስ ፕሮፌሰር መስፍን ምንም ሳይገባቸው እስከ አሁን አሉ። ለትውልደ-ትውልድ ማስተላለፍ (Posterity) በኢሕአፓ አብዮት የተካሄደና እየተካሄደ ያለ ጉዳይ መሆኑን ቢያውቁ ከፅንሐተ- ምሁራን ዘንድ ይመደቡ ነበር። አገር አከሸፉ ብለው ለመናገር ማን እንዳከሸፈ እያወቁ የአብየን እከክ ወደ እምዬ እንዳይሆን ያስተውሉ።

በመጨረሻም ለፈገግታ ያህል እንጂ ለኢሕአፓች ቁም ነገር ሆኖ ሳይሆን ያለፉ መሪዎች ፈሪዎች የሆኑበት ምክንያት ወላጅ አባቶቻቸው ወይንም እናቶቻቸው ስላላወቁ ተቀባይነት አይኖርም ብለው ይሆን የፈሩት። አሁንስ በኢትዮጵያና በኤርትራ ያሉት መሪዎች ይህን ፈርተው ይሆን አገር በአባትና በእናት እያሉ ሕዝቡን የሚያተራምሱ? ለዚህ ይሆን መታወቂያ በእናትና በአባት እያሉ ራሳቸውም ተጠልተው ሰውን የሚያስጠሉ። እርሶም ስለዚህ ጉዳይ ይበሉን ጨዋታውን ካመጣችሁት ማለቴ ነው። ፕሮፌሰር መስፍን ማን ናቸው፤ የአባትና የእናት አገርዎ ሊነግሩን ይችሉ ይሆን? ወይንስ ፕረሲደንት ኢሳኢያስ ሲጠየቁ የመለሱት ዓይነት ነው የሚነገሩን። መላ ሂወትዎ የትግል እንዳልነበረ እርስዎም እየመሰከሩ ኖት። አገሬ ኢትዮጵያ ናት ብቻ በተለይም በአሁኑ ሰዓት በቂ ምክንያት አይደለምና። አገራችን ኢትዮጵያ ናት ያሉትማ ተገደሉ፤ ተሰደዱና አሁንም ይባስ ብሎ እየታሰሩ ናቸው። ኢሕአፓማ ስለ አመጣጥም ሆነ፤ ዝርያ፤ ቋንቋም ሆነ ሃይማኖት ልዩነት ሳይፈጥር እንደ አያቶቹ ቅድም አያቶቹ የሕዝቡንና የአገሪትዋን ብሕራዊ ሴኩሪቲና ደህንነት ጠብቋል በመጠበቅ ላይም ነው ያለው። መክሸፍ የሚሉት ቋንቋ በኢትዮጵያዊም ሆነ በኤርትራ ምድር ላይ የተሰማሩ ኢሕአፓዎችን አይመለከትም። Put the blame where it belongs, Professor MWM!!!

ጥያቄና አስተያየት ካላችሁ

mailto:oboaradashawl@gmail.com?subject=Amharic proverb